አሜን ኢትዮጵያ
Amen Ethiopia

Amen Ethiopia
www.amenethiopia.com
info@amenethiopia.com

# ከአሜን ኢትዮጵያ የተስፋና የሰላም ተጓዦች ለኢትዮጵያውያን ሁሉ የቀረበ ጥሪ

የአዲሱ ሚሌንየም ጅማሬ ራሳችንን፣ ማኅበረሰባችንን እና አገራችንን መለወጥ እንችል ዘንድ መለስ ብለን ያለፈ ታሪካችንን እና አሁን ያለንበትን ሁኔታ ለመመልከት የተለየ አጋጣሚ ፈጥሯል።

የአሜን ኢትዮጵያ እንቅስቃሴ አነሳሾች በውጭ አገር የምንኖር ኢትዮጵያውያን ስንሆን የሦስተኛው ሺህ ዘመን መግቢያ ላይ የሠላም ጥሪ ለማስተላለፍ ከአሜሪካ - አውሮፓ በመኪና ወደ ኢትዮጵያ ከአርባ ቀን በላይ የፈጀ የተስፋ ጉዞ አደረግን። ይህን ታሪካዊ ጉዞ እውን ለማድረግ በተለያዩ አገሮች የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን እና ሌሎችም ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ ጊዜአቸውን እውቀታቸውና ገንዘባቸውን በማበርከት ትልቅ መስዋዕትነት ለከፈሉ ሁሉ ምስጋናችን ይድረሳቸው። በአካል ከእኛ ጋር ባይጓዙም በመንፈስ ከእኛ ጋር በመሆን አበረታትተውናል። በዚሁ በአዲሱ ሚሌንየም መባቻ የአሜን ኢትዮጵያ የተስፋና የሰላም መልእክት ይዘን አገራችን ስንገባ በኢትዮጵያ ሕዝብና በተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍል ተወካዮች ስለተደረገልን አቀባበልና መስተንግዶ እያመሰገንን ያገኘነው ሰፊ ይሁንታም የሚያበረታታ ነውና እንቅስቃሴአችንን እንቀጥላለን።

የተስፋ ጉዞአችንን ካጠቃለልን በኋላ በአፍሪካ አዳራሽ ውስጥ በተዘጋጀው የግንዛቤ ማስጨበጫ ስብሰባ ላይ የነበረው ሰፊ የሕዝብ ተወካዮችና መሪዎች ተሳትፎ እንቅስቃሴአችንን በትጋት እንድንቀጥል ከማበረታቱም በላይ ሕዝባችን ለሰላምና ለብሔራዊ መግባባት ጥማት እንዳለው አስገንዝቦናል። እንዲሁም በአዲስ አበባ ቆይታችንም ለአንድ ወር ያህል ጊዜ በተለያየ መድረክ ላይ የአሜን ኢትዮጵያን ዓላማ ለሕዝብ ከማስተዋወቃችንም ባሻገር ለበርካታ የማኅበረሰብ ክፍል ተወካዮችና መሪዎች ሰላምና ፍትህ ለማስፈን እንዲነሱ ጥሪ አስተላልፈናል። በተጨማሪም በተለያዩ የመገናኛ ብዙኃን የተሰጠን ሰፋ ያለ የዘገባ ትኩረት የአሜን ኢትዮጵያ ራዕይ በብዙዎች ዘንድ ተቀባይነት አግኝቶ ይህ ትንሽ ጅምር ትልቅ የጋራ ዓላማ ይሆናል ብለን እንድናምን አድርጎናል።

በኢትዮጵያ ሁለት ሺህ ዓመት መግቢያ ላይ በአሜን ኢትዮጵያ እንቅስቃሴ ዙርያ የተሰባሰብን በውጭ አገሮች ነዋሪ የሆንን የኢትዮጵያ ልጆች በኢትዮጵያ ከሚገኙ ወገኖቻችን ጋር ያለንን አንድነትና ትስስር ለመግለጽ እንወዳለን። ስለሆነም እኛ የሰላም ተጓዦች፥ በመንፈስ ከእኛ ጋር የተጓዙትንም ጨምሮ፣ ከደጋፊዎቻችን ጋር በመሆን ይህንን የተፈጠረልንን ይሁንታ በመመርኮዝ የአሜን ኢትዮጵያን አነሳሽ ዓላማ ቀጣይ ማድረግ እንችል ዘንድ ኢትዮጵያውያን ሁሉ ራዕያችንን በመካፈል ለሀገራችን ብልጽግና ለሕዝባችን ደህንነት በጋራ እንድንሠራ ጥሪ እናደርጋለን።

**Postal Address:** Rijksstraatweg 232, 1115 AV, Duivendrecht, Holland.

አሜን ኢትዮጵያ
Amen Ethiopia

Amen Ethiopia
www.amenethiopia.com
info@amenethiopia.com

የአሜን ኢትዮጵያ ዋና ዓላማ በኢትዮጵያውያን መካከል ኅብረትንና ብሔራዊ መግባባትን ማበረታታትና ሕዳሴ ኢትዮጵያ ሆኖ ሁሉም በመደማመጥና በመግባባብት፣ በመቀባበልና በመከባበር፣ በመተሳሰብና በመደጋገፍ ለአገር አንድነት፣ እኩልነት፣ እድገትና ብልጽግና በጋራ እንዲሠሩ ጥሪ ማድረግ ነው።

በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ አገሮች የምንኖር ኢትዮጵያውያን፤ በዚህ በሦስተኛው ሺህ ዘመን መግቢያ ላይ  ካለፈው ስህተታችን በመማር፣ ከታሪካችንና ከባህላችን ጎጂውን ጥለን መልካም በሆነው ላይ በመገንባት አገራችን በሁሉም መስክ የምትበለጽግበትን መንገድ መቀየስ ይገባናል። የሕዝባችንንም አብሮ የመኖር ፍላጎት የብልጽግና ጉጉት በምናጤንበት ጊዜ ሁላችንም የአቅማችንን ማበርከት እንዳለብን ህሊናችን ግድ ይለናል። ይህ ህዳሴ ኢትዮጵያን እውን ለማድረግ የሚጥር እንቅስቃሴ ዓላማው ግቡን ይመታ ዘንድ በሁሉም መስክ ተሰማርተው የሚሠሩ ወገኖቻችን፥ የመንግሥት አካላት፣ የፓለቲካ ፓርቲዎች፥ የሃይማኖት መሪዎች፣ የሙያ ማኅበራት፣ ምግባረ ሠናይ ድርጅቶች፣ እንዲሁም እያንዳንዱ ዜጋ ያላሰለሰ ጥረት ሊያደርግ ይገባል እንላለን።

በሰላም አብሮ መኖር ለእድገት መሠረታዊ ጉዳይ ነው። በሦስተኛው ሚሌንየም መግቢያ ላይ ኢትዮጵያ በተለየ መልኩ መስቀለኛ መንገድ ላይ ትገኛለች። አንድም ካለፉት ስህተቶችዋ ተምራ ጎጂውን ጥላ መልካም በሆነው ታሪኳ ላይ በመገንባት መጪው ዘመን ብሩህ እንዲሆን መሠረት ለመጣል ወደፊት መራመድ፤ ካልሆነም ደግሞ ያለፈውን ታሪክ መጥፎውን ጎን ብቻ በማጉላት እርስ በእርስ ወደ መለያየት ማምራት ነው።

አሜን ኢትዮጵያ ከየትኛውም ወገናዊነት ነጻ በመሆን በሁሉም የኅብረተሰባችን ክፍሎች ውስጥ በተለያየ መስክ የሚሠሩ ኢትዮጵያውያን ተቀራርበው በመነጋገር በልዩነት ምክንያት የሚነሱ ግጭቶችን ለመፍታት ጥረት እንዲያደርጉ ኢትዮጵያውያንን ይማጸናል። በኢትዮጵያ በሁሉም ብሔረሰቦችና የሃይማኖት ወገኖች ዘንድ ተቀባይነት ያላቸው ባሕላዊና መንፈሳዊ እሴቶችን በመጠቀም ቅራኔ ባለበት ቦታ ሁሉ ችግሮች በሽምግልና በመፍታት እርቅ እንዲሰፍን ጥረት ሊደረግ ይገባል እንላለን። እርስ በእርስ ተከባብሮ በመደጋገፍና በመቀባበል አብሮ በመኖር የሁሉም ብሔር ብሔረሰቦች፣ የሃይማኖት ወገኖችና የፖለቲካ ቡድኖች ፍላጎት፤ በስምምነት ተጠብቆ፤ በልዩነት ላይ የተመሠረተ ኅብረት የሚበረታታበትን መንገድ ለማመቻቸት አሜን ኢትዮጵያ የበኩሉን አስተዋፅዖ ያበረክታል። ይህ መልእክት የሚደርሳቸው ሁሉ ባሉበት የበኩላቸውን አስተውፅዖ እንዲያበረክቱም ጥሪያችን እናቀርባለን።

**Postal Address:** Rijksstraatweg 232, 1115 AV, Duivendrecht, Holland.

Amen Ethiopia
www.amenethiopia.com
info@amenethiopia.com

ለሰላም መሥራት የክርስትናም ሆነ የእስልምና ሃይማኖቶች መሠረታዊ መገለጫቸው ነውና በሀገራችን ፍትህ እንዲሰፍን የሃይማኖት መሪዎች የሚጠበቅባቸውን አስተዋፅዖ እንዲያደርጉ ተማጽነናል አሁንም ጥሪያችንን በድጋሚ ለሁሉም እናስተላልፋለን። በተለያዩ እምነት ተከታዮች መካከል መቀባበልና መከባበር እንዲኖር፣ ሁሉም የየራሳቸውን ውስጣዊ አንድነት ጠብቀው፣ በጋራ ጉዳዮች ላይ በመደጋገፍ ሕዝባችን በሥነ ምግባር እንዲታነጽ፤ ስለ ሰላምና አብሮ መኖር ትምህርትና ምክር በመስጠት በግልና በጋራ ጥረት እንድናደርግ ያሻል። እኛ የተሰፋ ተጓዦች በዓለም አቀፍ ደረጃ በሃይማኖት ተቋማት መካከል ትብብር እንዲበረታታ በአቋረጥናቸው አገሮች ሁሉ የሚገኙ የሃይማኖት መሪዎች ጋር በመገናኘት የሀሳብ ልውውጥ በማድረግ ስለሰላምና ፍቅር በመስበክ ለፍትህና ጽድቅ እንዲቆሙ ተማጽነናል። በተለይም በአሁኑ የዓለማችን የሰላም ሁኔታ በተናጋበት ወቅት፣ ስለሰላም እና እርቅ ድምፅን በማሰማት የመግባባትና የእርቅ አዲስ ምዕራፍ በኢትዮጵያ ከተዘረጋ ለአፍሪካ ቀንድ ችግርም መፍትሔ ፈር ለመቅደድ ይቻላል ብለን እናምናለን።

የተሰፋ ተጓዦች ሁሉ የራሳቸውን የግል ቁስል ለተሻለ የወደፊት ክፍት በማድረግ እና ከሌሎች ጋር አብሮ ለማደግ የሚጥሩበት የፈውስ ጉዞ ጅማሬ ነው። ከተሰፋ ጉዞው ቀደም ብሎ በአውሮፓና በአሜሪካ ከምሁራን ጋር የተደረጉ ዐውደ ጥናቶች ስለዓላማችን ግንዛቤ እንዲኖረን እረድተውናል።፡ በጉዞአችንም ሂደት ውስጥ ካገኘናቸው ወገኖቻችን ጋር ስላገኘነው ልምድና ስለዓላማችን በተቻለን መጠን ውይይት አድርገናል። በውጭ አገርና በአገር ውስጥ በሚገኙ ኢትዮጵያውያን መካከል መግባባት እንዲሰፍንና ሁሉም ለአገራችን እድገትና ብልጽግና አዎንታዊና ገንቢ በሆነ መልክ በመሳተፍ የበኩላቸውን ማበርከት ይጠበቅባቸዋል። ይህን ለመተግበር መሪ ቃሎቻችን ማስተዋል፣ መተሳሰብ፣ መደማመጥ፣ መግባባትና መቀባበል መሆን አለባቸው።

በአሜን ኢትዮጵያ ዓላማ ዙሪያም አገራችን ውስጥ ቀጣይነት ያላቸው ተግባራት ለማከናወን ልምድና ትብብር እናገኝ ዘንድ ከተለያዩ በውውይት ዘዴ ዙርያ ልምድ ካላቸው ተቋማት ጋር ምክክር አድርገናል። በደረስንበት ሁሉ አገራችን ያሏትን በረዥም ጊዜ የተካበቱ መልካም ባህላዊና መንፈሳዊ ገጽታዎቿን ከፍ አድርገን በማሳየት ለዓለም ኅብረተሰብ አስተዋውቀናል። በዚህች ምድር ነዋሪ ለሆኑ ሁሉ የወደፊቱ ሕይወት ብሩህ የሚሆንበትን እና ፍትህ የሰፈነበት ዘመን ለመፍጠር፣ በትክክለኛው አቅጣጫ ለመጓዝ ሁሉም የበኩሉን አስተውፅዖ ያበረክት ዘንድ በተስፋ ጉዞው ሂደት ውስጥ ሁሉንም ተማጽነናል።

አሜን ኢትዮጵያ
Amen Ethiopia

Amen Ethiopia
www.amenethiopia.com
info@amenethiopia.com

እኛ በአሜን ኢትዮጵያ ዓላማ ዙርያ የተሰባሰብን ወገኖች የተስፋ፣ የሰላም፣ የእርቅና የመለወጥ መልእክታችን እንዲደርሳችሁ እንሻለን። የወገናችንን ሊገመት የማይችል የሰላም ጥማትና ለእውነተኛና ዘላቂ እርቅ ያለው ጽኑ ፍላጎት ለአገር ብልጽግናና እድገት ያለውን ውስጣዊ ፍላጎቱን ያንጸባርቃል። የኢትዮጵያውያን አንዱ መለያ የሆነ የብዙ ባሕሎችና ሃይማኖቶች ባለቤትነትን እውነታ ማጤን፣ በመግባባት የሚደረግ ውይይት ለሰላም ጠንካራ መሠረት፣ ለሥልጣኔና ለብልጽግና ብቸኛ አማራጭ መሆኑን መገንዘቡ እጅግ ጠቃሚ ነው። ይህ የወደፊቱን ከማመቻቸት ባሻገር በታሪካችን አለመግባባትንና ግጭትን ካስከተሉ አምባ ገነናዊ አካሄዶች እንድንማር ይጋብዘናል።

ዛሬ በአገር ደረጃ የተለያየ አመለካከት ያላቸው ሁሉ ተቀራርቦ በመነጋገር ብሎም በመግባባት ለጋራ እድገት ሊሰለፉ ይገባል።፡ ለአገራችን የዛሬ ሁኔታና የነገ ኅልውና ከልዩነት ለሚመነጩ ግጭቶች እያንዳንዳችን በተናጠልና በጋራ መፍትሄ ለማምጣት ጥረት ማድረግ ይጠበቅብናል። በሁሉም ብሔረሰቦች ዘንድ ተቀባይነት ያላቸውን ኢትዮጵያዊ ባሕሎችና ወጎችን መሠረት ባደረጉ ልምዶች የመቀራረብንና ለጋራ እድገት አብሮ መሥራትን ልናበረታታ ይገባል። በሃይማኖት ተቋማት መካከልም የሚደረገው ትብብር የኢትዮጵያን ዋነኛ ችግር ለመቅረፍ ትልቅ አስተዋፅዖ ማበርከት ይችላል።

ከመቼውም ጊዜ በላይ ጠንካራ የሆነ አብሮ የመኖርን የወንድማማችነትን መንፈስ፣ የራስ ተነሳሽነትን እና የውስጣዊ ለውጥ ጥልቅ ፍላጎት አስፈላጊነት መገንዘብ ወሳኝነት አለው። ምንም እንኳን ከእይታችን ብዙ የራቀ ቢሆንም ካለፈው ታሪካችን ጋር ለመታረቅ፣ ጠባሳ የተዉትን ለትውልድ በታሪክነታቸውና በአስተማሪነታቸው በማስተላለፍ፤ በጎ ገጽታዎቹን ማድነቅና መረዳት እነዚህንም አግብሮ በቀጣይነት ይዞ መራመድና በእነሱም ላይ መገንባት አስፈላጊነቱ ይታየናል። ብዙ ውጣ ውረድ የበዛበት የአሜን ኢትዮጵያ የሰላም ጉዞ ኢትዮጵያ በሦስተኛው ሚሌንየም ለለውጥ በምታደርገው የተስፋ ጉዞ የምታልፍበትን የአዲስ ምዕራፍ እንቅስቃሴ ያመላክታል።

ይህ የአዲሱ ሚሌንየም አከባበር በሕዝባችን መካከል የሚታየውን ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ይዞታዎች የተራራቀ ልዩነት ለማስተካከል፤ እንዲሁም ያለምንም ብሔር ብሔረሰብ፣ ሃይማኖት፣ ጾታ ልዩነት ለሁሉም እንደሰብአዊ ፍጡርነቱ የሚገባውን ከበሬታ መሰጠት እንዳለበት የሚያሳስብ ጥሪ ለማስተላለፍ ድምፃችንን የምናነሳበት አጋጣሚ ፈጥሮልናል።

**Postal Address:** Rijksstraatweg 232, 1115 AV, Duivendrecht, Holland.

አሜን ኢትዮጵያ
Amen Ethiopia

Amen Ethiopia
www.amenethiopia.com
info@amenethiopia.com

የአዲሱ ሚሌንየም መባቻ በኅብረተሰባችን መካከል በመቀባበል አብሮ የመኖርና ሰላምና ፍትህ ላይ የተመሠረተ እድገት ለማምጣት፣ በቁርጠኝነት ሁላችንም የምንሰለፍበት ጊዜ መሆን ይገባዋል። በተለይም ስለአገራችን ሰላምና ብልጽግና ሁሉም በያለበት አቅሙ በፈቀደ መጠን የድርሻውን ከማበርከት ወደኋላ እንዳይል ልባዊ ጥሪያችንን ማስተላለፍ እንወዳለን። ”አሜን” እውነት ማለት ነው። አሜን አበው ሲመርቁን ምርቃቱ በእውነት በእኛ ላይ እንዲፈጸም የምንሰጠው ምላሽ ሆኖ፣ መቀበልንና መቀባበልን ያመለክታል ለአዲሱም ዘመን መግቢያ የተሰፋ ቃል ነው።

ይህ ትንሽ ጅምር ትልቅ የጋራ ዓላማ ነውና ራዕያችንን እንዲጋሩ በጎ ፈቃድ ያላቸው የኢትዮጵያ ጉዳይ ይገደኛል የሚሉ ሁሉ  መርሐግብራችንን እንዲደግፉ ወይም ሌላ መሰል እቅድ በመንደፍ ለአገራችን ሰላምና ለጋራ ብልጽግና እንዲሠሩ ጥሪአችንን እናስተላልፋለን።

አምላክ አገራችንን በሰላም ሕዝቦቿንም በአንድነት ይጠብቅልን!

የአሜን ኢትዮጵያ የተስፋ ተጓዦች

**Postal Address:** Rijksstraatweg 232, 1115 AV, Duivendrecht, Holland.